# አሸባሪነት እና ሚዲያ

**(ዮሀንስ አልታሞ)**




የሚዲያ ተቋማት ለተደራሾቻቸው የሚያቀርቡት ዜና ትኩስ እና ትኩረት ሳቢ እንዲሆን ከፍተኛ ፉክክር ላይ ይገኛሉ ። የቀዳሚ ዜና ምንጭነት ትልቅ ዋጋ የሚከፈልበት የሚዲያ ውጤት እየሆነ መጥቷል። ለዚሁ ሲባል ጋዜጠኞች ለገዛ ህይወታቸው አስጊ የሆኑ የጦርነት ቀጠናዎች ሳይቀር ገብተው ይዘግባሉ፣ ዘጋቢ ፊልሞችን ለመስራት የሚያስችሉ መረጃዎች ይሰበስባሉ። የሰላም ዜና ከዜናነት ተርታ እየወጣ በአንጻሩ የሁከት እና የሽብር ዜና የዘወትር አርዕስተ ዜና ሆኗል። የልማት እና ዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እና ትግበራ እንቅስቃሴዎች እንደ ዋና ዜና ሳይሆኑ እንደተደማሪ መረጃ መታየት ጀምረዋል። የሰው ጀሮ አዎንታን ሳይሆን አሉታን መከታተል መርጧል። ሚዲያዎቹም ይሄንኑ ፍላጎት የሚያሟላ መረጃ ማነፍነፍን ተያይዘውታል። ይህ የሚዲያዎች ቅኝት ለአሸባሪዎች አላማ ማስፈፀሚያ ሁነኛ እድል ፈጥሮላቸዋል።

በመሆኑም የሽብር ድርጊት ሲፈፀም የሚዲያ ተቋማት በአቅራቢያ መኖራቸውን አሸባሪዎች እንደሚያረጋግጡ ጠቋሚ ሁኔታዎች ይስተዋላሉ ። ሚዲያ ሳይኖር የሚፈጸም የሽብር ድርጊት የለም። በአብዛኛው የአሸባሪዎች የጥቃት ኢላማ በሽብር ድርጊት ህይወታቸውን የሚያጡ ንፁሀን ዜጎች ሳይሆኑ በአንጻሩ ጥቃቱን ተከትሎ የሚፈጠረው አጠቃላይ የደህንነት ስጋት ብሎም መንግስት ከህዝብ ጋር የገባውን ኮንትራት ጥያቄ ውስጥ ማስገባቱ ነው። ለዚህ የሚዲያ ተቋማት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። የአሸባሪዎች እና የሚዲያ ተቋማት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የእኩል ተጠቃሚነት

አይነት ግንኙነት አላቸው። እልቂት አዘል የሚዲያ ውጤት የሚያቀርብ የሚዲያ ተቋም በገበያ የሚኖረው ተፈላጊነት ከፍተኛ ነው። ለዚህ ደግሞ መጋቢ ተግባር የሚፈጽሙ አሸባሪዎች የሽብር ድርጊቶቻቸውን አለም በጠቅላላ እንዲያውቅ ያላቸውን ፍላጎት ያለ ውጣ ውረድ ያሟሉበታል። በመሆኑም ይህ አደገኛ ትስስር ለአለም መንግስታት የእራስ ምታት ከሆነ ሰነባብቷል። በዚህም ምክኒያት መንግስታት በአስተዳደር ክልላቸው የሚንቀሳቀሱ የሚዲያ ተቋማት በተቻለ መጠን ነፃነታቸውን ጠብቀው የህዝባቸውን ሰላምና መረጋጋት በሚያውኩ ዘገባወች እንዳይጠመዱ የሚከለክል የሚዲያ ህግጋትን ያወጣሉ። ሀላፊነት የጐደለው እና ትርፍን ብቻ የሚያሳድዱ እንዳይሆኑ በስርአት እንዲመሩ ያስገድዷቸዋል። አንድ አንድ መንግስታት ደግሞ በአንፃሩ ድርድር የማያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ቀይ መስመር አስምረው ከተቋማቱ ጋር የጋራ መግባባት ፈጥረው ይንቀሳቀሳሉ።

ከዚህ አንፃር በታዳጊ አገራት የሚገኙ ሚዲያዎች ከመንግስታት ጋር የሚያደርጉት እሰጣ ገባ ፈር ባለመያዙ ጋዜጠኞች ለእስር እና እንግልት የመጋለጥ እድላቸው የሰፋ ነው። እንደዚህ አይነት ሁኔታ በአብዛኛው በአፍሪካ አገራት የሚስተዋሉ ክስተቶች ናቸው። ለዚህ የአፍሪካም ሆነ የሌሎቹ መንግስታት ምላሽ ጋዜጠኞች በሙያቸው ሳይሆን ለሽብር ድርጊት ባሳዩት ተባባሪነት እና አጋርነት መጠየቅ ይኖርባቸዋል የሚል ሲሆን ጋዜጠኞች እና ለጋዜጠኞች ጥብቅና ቆመናል የሚሉ አካላት ደግሞ ከመናገር፣ከመጻፍ እና ሀሳብን በነጻነት ከመግለጽ ጋር ያያይዙታል።

“ያለ ሚዲያ ሽፋን የሽብር ድርጊት ለአሸባሪዎች ኪሳራ ነው። ለአሸባሪዎች ትልቁ ግብ በፈንጂ ጉዳት የደረሰበት ሳይሆን ሰፊው የጥቃቱ ተመልካች የሚያሳየው ምላሽ ነው። ቡድኑ በጦርነት ላይ ነው፣ ግማሹ ጦርነት የሚካሄደው አሊያም የጦር ሜዳው ሚዲያ ነው” የአልቃይዳው መሪ ሆሳማ ቢላደን በአሜሪካ ኮማንደሮች ከተገደለ በኋላ ቡድኑን ሊመራ የተመረጠው አይመን አል-ዘዋሪ የተናገሩት ።

የሚዲያ ይዘት እና አይነት በጊዜ ሀደት ተቀያይሮአል። ከበርሊን ግንብ መፍረስ እና የሶቪየት ህብረት መፈረካከስ በኋላ የተፈጠሩ የቴክኖሎጂ ክስተቶች እና ለውጦች የግኑኝነት እና መረጃ ልውውጥ ሁኔታን ቀያይረውታል። የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች በኢንተርኔት እና በሞባይል ስልኮች ስርጭት ምክንያት ተደራሽነታቸው የሰፋ ከመሆኑም በተጨማሪ መረጃን ለህዝብ የሚያቀርብ አካል ውስንነትን ከስረ መሰረቱ ቀያይሮታል። ዛሬ አንድን መረጃ ለመዘገብ የጋዜጠኝነት ሙያተኛ መሆን የግድ አይልም። የእነኚህ ቴክኖሎጂ እድገት አሸባሪዎች ድርጊቶቻቸውን በቃላት እና ምስል አስደግፈው

የተለየ ጋዜጠኛ እና ሚዲያ ሳያስፈልጋቸው ለተቀባይ ሚዲያዎች እና ለተደራሾቻቸው ያስተላልፋሉ። በዚህም ፕሮፖጋንዳ ስራዎቻቸውን በተሳለጠ መልኩ ይሰራሉ አባላት ይመለምላሉ።

ስለ ሚዲያ ተቋማት እና ጋዜጠኝነት ስናወራ፣ስንጽፍ እንዲሁም ስናነብ ይህች የምንኖርባት አለም ያለ እነሱ ሙያ እና ተቋም ምንኛ ጎስቋላ እንደምትሆን መገመት አይከብድም ። በአንደኛው የአለም ጫፍ ያሚገኝን መረጃ ወደሌላኛው በማድረስ ፣የመረጃ ረሀብተኛ የሆነውን የ 21 ኛው ክፍለ ዘመን ሰው በመረጃ በማጥገብ ለአለም ኢኮኖሚ ውህደት እና እድገት ፣የፓለቲካ አስተሳሰብ እና ደህንነት ትልቅ አስተዋፅጾ አላቸው ። አስተዋፅጾ ደግሞ በህይወት መስዋዕትነት የታጀበ ጭምር ሆኖ ይስተዋላል። እ.ኤ.አ በ 2004 ዓ.ም ለጋዜጠኞች የከፋ አመት ሆኖ የተመዘገበ መሆኑን በወቅቱ የአለም አቀፍ የጋዜጠኞች ፌዴሬሽን IFJ እሳውቋል ። በዚህም በዚያ አመት ብቻ በተለያዩ አገራት ስራ ላይ ተሰማርተው ውድ ህይወታቻን ያጡ ጋዜጤኞች እና የሚዲያ ሰራተኞች በቁጥር 129 መድረሱን ገልጾ ነበር ። በኢራቁ ጦርነት ብቻ ሀምሳ ጋዜጠኞች አልቀዋል ።

ከዚህ የጋዜጠኝነት ለአደጋ ተጋላጭነት ባሻገር መንግስታት የሚፈልጉትን አጀንዳ በሚፈልጉት ህዝብ ላይ ለማስረጽ እና በአጀንዳው ዙሪያ በርካታ ደጋፊ ለማሰባሰብ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ በሆነ መንገድም ሲጠቀሙባቸው ይስተዋላል ። በተለይም ምዕራባውያኑ ከዚህ አንጻር ተጠቃሽ ናቸው። መንግስታቱ በሌሎች አገራት መውሰድ ለሚፈልጉት እርምጃዎች እና ጣልቃ መግባቶች ሁሉ ምክኒያት እና መንስኤ የሚሆኑ መረጃዎችን እና ትንታኔዎችን በመፍጠር መንገድ የመጥረግ ሚና እዲወጡ ያስታጥቋቸዋል።

በሌላ በኩል የመናገር ፣የመጻፍ እና ራስን የመግለጽ መብት የሰብአዊ ፍጡር የመብት ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን የሚናገረውን አትናገር፣የሚጽፈውን አትጻፍ ፣ሀሳቡን በመሰለው መንገድ የሚገልጸውን አፍህን ያዝ ማለት የማይቻልበት የዲሞክራሲ ዘመን ላይ የምንገኝ ሲሆን ፣ የሚሰራጩ ዜናዎች እና የሚበተኑ መረጃዎች በማወቅም ባለማወቅ የሽብር ቡድን ግቦችን በቀላሉ የሚያሳኩ መሆኑ እዲሁም የጋዜጠኝነት እና የሚዲያ ፕሮፌሽናሊዝም ጉዳይ የተፋጠጡበት የመረጃ ጦርነት ዘመን ላይ እገኛለን። በአንድ ወገን መረጃውን ልቀቅልኝ የሚል የመረጃ ረሀብተኛ ፣በሌላ በኩል የሚለቀቀው መረጃ የሶስተኛ ወገን ግብ ማሳካቱ ፣በመሀከል ህዝብን ለማስተዳደር የተቀመጠ መንግስት እና መረጃ አሰራጭ አካላት (ሚዲያው )የገቡበት ፍጥጫ እውነተኛ የመረጃ ጦርነት ያስብላል ።

አሸባሪዎች በካይሮ፣ስቶክሆልም፣ለንደን፣በርሊን፣ኦርላንዶ፣ብራሰልስ፣እስታንቡል፣ባግዳድ፣አንካራ ፣ፓሪስ... ወዘተ የፈጸሙት የሽብር ጥቃት በጥቂት ደቂቃዎች አለም በአንዴ እንዲሰማ እና እንዲደነግጥ ከማድረጉም ባሻገር ቀጥተኛ ተጠቂ አገራትን ጨምሮ ሌሎች የደህንነት ህጎቻቸውን ዳግም እንዲያጤኑ ገፋፍቷል ። ለዚህ የሚዲያው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። አሸባሪዎች የፈጸሙዋቸውን አስፈሪ እና አሳፋሪ ድርጊቶች ለአለም ደጋግሞ በማሳየት የፍርሃት እና ሽብር ስሜት እንዲፈጠር በማድረግ ያለ ውል የተጀመረውን የሚዲያ -አሸባሪዎች የጥቅም ተጋሪነት ከውነውታል።

ሚዲያው ለአሸባሪዎች ትርፍ የሚያስገኝ እንቅስቃሴ ውስጥ አውቆም ሆነ ሳያውቅ ከገባ እዴት መውጣት ይችላል? ይሄን ጥያቄ ለመመለስ የተለያዩ መንግስታት ከሚዲያ ተቋማት እና ጋዜጠኞች ጋር ከላይ እንደተመለከተው እሰጣ ገባ ውስጥ ይገባሉ ። ለዚህ የሚዲያ ስራ እና ሽብር ተግባር አደገኛ ኢ-መደበኛ ትስስር ትክክለኛ እና ቀና የሆነ ምላሽ ለመስጠት ግን የሚዲያውን የገበያ ትኩረት በስነምግባር እሴቶች እንዲገነባ ዘርፈ ብዙ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። አንዳች የሽብር አደጋ ከተከሰተ እንዲሁም የሚከሰትበት አዝማሚያ የሚኖር ከሆነ ፣ ከሽብር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ማናቸውም ግኑኝነቶች እና እቅስቃሴዎች በሚዲያ ወይንም በጋዜጠኛ አይን ውስጥ ከገባ የቀዳሚ ዜና ምንጭነት አባዜ እና የገበያ እሽቅድድም የዘመነኞቹ ሚዲያ ቅኝት በሆነበት የዘገባዎቹን ይዘት እየተከታተሉ ፍጥጫ ውስጥ መግባቱ ለጉዳዩ ዘለቄታ ያለው መፍትሄ አይሆንም። አንድ አንድ መንግስታት ደግሞ ሳንሱር ማድረግን የጸረ ሽብር ዘመቻ አካል አድርገውም ይወስዳሉ ።

በአጠቃላይ መንግስታት የሚያራምዱት የጸረ ሽብር እንቅስቃሴ የመናገር፣የመጻፍ እና ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን እንዳይገድብ ሚዲያዎቹ ራሳቸውን ሳንሱር እያደረጉ ፣መረጃ የሚሰጡትን ህብረተሰብ በታላቅ ስነምግባር በማክበር ስራቸውን እንዲያከናውኑ ነጻ መብት መስጠት ያስፈልጋል።

ያለ ፍላጎት እና ኮንትራት የአሸባሪ ቡድኖች ቃል አቀባይ የሆኑ ሚዲያዎች በርካቶች አሉ ። አሸባሪዎች ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ መሳካት አስተዋዕጾ የሚያደርጉ ሚዲያዎች የቃል አቀባይነት ሚና እየተጫወቱ እንደሆነም ልብ ሊሉ ያስፈልጋል።

በአገራችንም መንግስት በሚዲያው ዘርፍ የጀመራቸውን ስራዎች አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። የተለያዩ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በመከፈት ላይ ናቸው፣ከዚህ ቀደም ያልነበሩ ጋዜጦች እና መጽሄቶችም ብቅ ማለት ጀምረዋል። ሆኖም ከጥቂት አመታት በፊት የነበረው የሚዲያ ዘርፉ መነቃቃት ተመልሶ እንዲመጣ የተጠናከረ ስራ መስራት ያስፈልጋል። ከዚያም የተሻለ። ሆኖም የህብረተሰቡን ሞራል

የሚጠብቁ መረጃን ሳይፈሩ እና ሳይሸማቀቁ ማቅረብ የሚችሉ ነጻ ሚዲያዎች መፈጠር ይኖርባቸዋል። የመንግስት ተቋማትም የሚጠይቋቸውን መረጃዎች ሊሰጧቸው ይገባል።

ቸር ይግጠመን